# አይናችንን ገልጠን እንጸልያለን

የኬኒያው ጆሞ ኬንያታ እንዲህ አሉ ይባልላቸዋል፦

"አውሮፓዊያን ሚሺነሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ይዘው መጥተው አጎንብሳችሁ ጸልዩ ሲሉን ለሙ መሬት በእጃችን ነበረ፡ ጸልየን ስንጨርስ ለሙ መሬታችን እነርሱ እጅ ሆኖ ፤እኛ እጅ መጽኃፍ ቅዱስ ብቻ ቀርቶ ነበር"

እኛም እንዲህ አልን " ሓይማኖት በፓለቲካ ፓለቲካም በሃይማኖት አይገባም አሉን ቀጠሉና እናንተ ዝም ብላችሁ ጸልዩ ሲሉን ፤ አጎንብሰን መጸለይ ጀመርን፡፡ ቀና ስንል ያሉን ነገሮች በሙሉ ኪሳችን የነበሩ ሳንቲሞች ሳይቀር በሙሉ ሄደው ፓለቲከኞች ሂሳብ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው አየናቸው ፡፡

እግዚአብሔርን እየፀለየ የሚያመልክ በትክክለኛ ጎዳና የኖረ ህዝብ ሳይሆን ሲያጎነብስ ምግቡ የተነሳበት አማኝ የመሰለ ረሃብተኛ ህዝብ ይዘን ታቅፈን ቀርተናል፡፡ እየመራን ያለነው ህይወት ግራ አጋቢ ሆኖብናል፡፡ ሰሞኑን በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ለንባብ እንደበቃው ሰሞኑን ስልጣናቸውን ለለቀቁት የሐገራችን ፕሬዘዳንት የመኖሪያ ቤት ኪራይ ውል እንዲፈርስ ተደረገ እንዳሉን የፈረሰው ውል ወርሃዊ የቤት ኪራይ የኪሳችን ሳንቲሞች የት ደርሰው ተከምረው እንደሆኑ የሚያሳዩ ነበር ብር 350,000.00 ወርሃዊ ኪራይ እንዲከፈል ውል የተፈጸመበት ሲሆን አሁን ውሉ ፈርሶአል ሲል አስታውቆናል፡፡ በመጨረሻ ላይ እነዚህን ቁጥሮች እናያቸዋለን፡፡

ለጸሎት ባጎነበስንበት ቀና ስንል ሌላው ቀርቶ ምድር የእግዚአብሔር እንደሆን ስናምን ለነበርን ቤት መስሪያ መሬት እምነታችንን የምናከናውንባቸውን ቦታዎች እስከናጣ ድረስ ከእጃችን ርቀው ሄደው ፓለቲከኞችን ስንለምናቸው ራሳችንን አግኘተናቸዋል ፡፡ ምን ማሰብ ምን አለማሰብ እንዳለብን እንዲገሩን ካልሆንም ዝም ልንል ጸሎቱንም ቃላቶች ስንመርጥ እየተመረጡ እያጠሩ እያጠሩ እያጠሩ በቴሌቪዥን የምንሰማውን ያለስጋት የምንናገራቸው ኪራይ ሰብሳቢ ልማታዊ የህዳሴ ግድብ ወይም ትራንስፎርሜሽን እያልን ልንደግም ስንዘጋጅ እራሳችንን አግኝተናል …

.ከዚያ በሁዋላ አይናችንን ገልጠን ከመጸለይ ውጪ ጨፍነን በምንጸልይ ጊዜ ምን ሊደረግ እንደሚችል ወደማናውቅበት ሁኔታውስጥ እራሳችንን አይተነዋል! አሁን ያለን አማራጭ የሚያደርጉትን አይናችንን አፍጥጠን ማየት ብቻ ነው!

ድህነቱ የት እንዳደረሰን በዚህ ዘመናዊ አለም ውስጥ ከምድር መጨረሻ የሆንባቸው እውነታዎች መነሻቸው አንድና አንደ ብቻ ከሙኖን እንዳላለፉ መገንዘብ እንችላለን ፡፡ ይህም የሓይማኖት ቤቶች ሓይማኖተኛ ህዝባቸው ላይ የወደቀውን ድህነት መነሻ ምክንደያቱን በመፈለግ ፋንተ ፓለቲከኞች የሚያወርዱላቸውን ዜማ እየተከተሉ ሲያዜሙ መኖራቸው ሲሆን ፡፡ ፓለቲከኞችም ሆነ ሓይማኖተኞች ከስብከታቸውም ሆነ ከቲየሪዎቻቸው ቀጥሎ በተግባር የሚደረጉ የጋራ ህግ ህገመንግስት በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን ባለመቆጣጠራቸው ህግ ዘለል ጉልበተኞች ሓገርና ህዝብን ድሃ ማድረጋቸውን ማየት አለመቻል አደጋውን ቤታችን ውስጥ አድርገውታል፡፡

እናም ሰይጣን ወደ ምድሪቱ የላካቸውን የመርገም መልእክተኞችን ቀጥ ብለን እያንዳንዱን ጉዳዮች ካላየን ለማስተካከል ካልተነሳን በብዙ እጥፍ በከፍተኛ ፍጥነት መሄዳቸው የማይቀር ስለሆነ ጸሎታችን ከቤትና ከጉዋዳችን አልፈው ሃገር ካልተባረከች በዘመናዊ አለም ውስጥ ታሪካዊ ተጠያቂዎች እንደሆንን ማሰብ ይኖርብናል፡፡ ሃገር የሚባለው ፕሬዘዳንታችን ብቻ ሳይሆኑ የሚመሩት ህዝባቸውም ጭምር ሲሆን እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ ሲሉ የቆዩት ፕሬዘዳንታችን የራሳቸውን በረከት ብቻ ከሆነ ይዘው የሄዱት ምንም እንኩዋን የሳቸው መሪ ባይሆን የክርስቲያኖች መሪ ኢየሱስ ከሄደበት በተቃራኒ መንጎዳቸውን ግን መገንዘብ እንችላለን፡፡ ኢየሱስ እራሱን አላስደሰተም ኢየሱስ ለራሱ አልኖረም ኢየሱስ ለድሆች የምስራች ይዞላቸው እራሱን አሳልፎ ሰጥቶላቸዋል!

ይሄ ሁሉ ድህነት የመጣው ከተከተልነው ፓለቲካና ፓለቲከኞቻችኝ አጥበውን እንደሆነ ማየት እንችላለን፡፡ አሁን ፓለቲከኞች የሚሰሩትን አይናችንን ገልጸን እያየን እንጸልያለን በየትኛውም አይነትና ጎራ ሊሆኑ ይችላሉ መሰረታችን ህገመንግስት እንጂ የፓለቲካ ፓርቲዎች መርሃግብር የኛ ሊሆን አይችልም፡፡ የኛ የሆነው እግዚአብሔር ምድራችን የአንድነት የፍቅር የእኩልነት ድሆች እንደገና ድሆች ሆነው የማይቀጥልበት ከቀማኞች ምድራችንን እንዲያድን ሠይጣን የጥፋት እጁ እንዲገታ የምናዝበት ሰዓት ላይ ነን፡፡ ይህም ፓለቲከኞቹንም ይጠቅማቸዋል!

ለመሆኑ ፖለቲካና ፓለቲካ ምንድን ነው ?

ፖለቲካና ፓለቲከኛ

- የሃገርን ስልጣን ይዞ ህዝብን ለማስተዳደር የሚጠቀምበት የማስተዳደር ዘይቤው ስሙ ነው
- ልክ ቁጥርን ማስላት ሂሳብ እንደሚያስተምረን ምስልን በወረቀት ላይ ማውጣት የሚቻልበትን የፎቶግራፍ ጥበበ እንደሚያስረዳን የመንግስ አስተዳደር ምን መምሰል እንዳለበት ስሌትን የሚፈልግበት ትምህርት ስሙ ነው:፡ ፖለቲካ እንደ አንድ የትምህርት አይነት በሳይንስንት የምንማረው ማለት ነው። የማስተዳደር ዘይቤዎችን መርሆዎችን ከታሪክ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማያያዝ ጥቅምና ጉዳትን የሚመዝን ትምህርትን ለማለት ነው
- የሃገርን አስተዳደርን ሃላፊነትን የያዘ ሰው እራሱን የሚጠራበት የሙያ መጠሪያ ነው ፖለቲከኛ
- የግል ስራን ውጤታማ ለማድረግ የሚኬድ አካሄድ ፖለቲካ ሊሆን ይችላል።ስልጣንን ለመያዝ የሚደረግን ውጥን/አካሄድን በንግድ በስፖርት በሙዚቃ ወይም በቤተክርስቲያን ሊሆን ይችላል አካሄዱ ራሱ ፖሊተካ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። የአንተ አካሄድ ከእኔ *Your politics are clearly more liberal than mine.ለይነት ማለት ይቻላል፡፡*

**ክርስትና ከፖለቲካ ጋር ግንኙነት አለው?**

በእርግጥ ክርስትና ፓለቲካ ያለበት እምነት ነው፡፡ ፓለቲካ የሌለበት ሃይማኖት በምድር ላይ አልነበረም መኖርም አይችልም፡፡ ስርዓት ያለው በአስተዳደር የሚመራ እምነት ለማለት ነው፡፡ ሰውን ማስተዳደር የሚችል ህዝብን ማስተዳደር የሚችልና በማስተዳደር ጊዜ ሊፈጠሩ የሚችሉትን ጉዳዮች በሙሉ ስርዓት ባለው መንገድ የሚያስተናግድ መዋቅርን መስራት የሚችል በመዋቅር የሚመራ ስለሆነ ፓለቲካ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዲሞክራሲያዊ ነው አይደለም የሚለውን በጥያቄ ውስጥ አስቀምጠን፡፡

እስኪ ትንሽ እንየው አብረሃም ይስሃቅ ያቆብ በቤተሰብ ደረጃ አስተዳዳሪዎች የነበሩ ሲሆን የሴፍና ሙሴ ነጻ አውጪ መሪ ዎች ነበሩ ፡፡ የሴፍ ከረሃብ ሙሴ ከባርነት ህዝባቸውን ነጻ አውጥተዋል፡ ከረሃብ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ከ ባርነት የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚለውን ስም በማስተዋወቅ አዝማች በመሆን የሚወጡበትን መንገድ የሚያቅድ የሚያጠና የሚያማክር የሚያዝ የሚያስኬድ የሚመሩትን የሚመርጥ የሚያስመርጥም ነበረ....ሙሴና የሴፍ ፖልቲከኛ ካልተባሉ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት እራሱ ይከብዳል ፡፡ ወደ ዳዊት ስንመጣ ይህን ሁሉ ሙሴ ያደረገውን ማከናወን ብቻ ሳይሆን በፓለቲካው ስራ ተጠምዶ በቤተመቅደስ የሚቆይበት ጊዜ አጥሮት አንድ ሺ ቀን በቤተመንግሰት ከመሆን አንድ ቀን በቤተመቅደስህ ደጃፍ በሆንኩኝ ይል ነበር ከመዝሙረ ዳዊት ፡፡ መዝ 84፡10

በሌላ ስፍራ አንድ ሺህ ቀን ከመቈየት<br>
በመቅደስህ አንድ ቀን መዋል የተሻለ ነው፤<br>
በክፉዎች ቤት ከምኖር ይልቅ<br>
በእግዚአብሔር ቤት ዘበኛ ሆኜ መኖርን እመርጣለሁ።

እንደምታውቁት ዳዊት መቅደስ የሚያውል ስራ ሳይሆን ሌላ ስፍራ ነበር የሚያውለው ውጊያ ሲመራ ዲፐሎማቶች ሲልክ ህዝብ ሲያስተዳደር መከላከያ ሲገነባ ግብር ሲያሰባስብ ህዝብ ሲቆጥር ሲያስቆጥር ጎልያድን ሲጥል ነበር ንጉስ ዳዊት እንደልቤ የተባለው!

ይህንን ጉዳይ በዮሴፍ በግብፅ ላይ የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረ በንጉስ በሰለሞን ወይም በነቢዩ ዳንኤል (120 አገሮች ላይ የተሾመ) ወይም በነቢዩ ሚኪያስ ወይም በሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች አስተዳደሮች መልካም እንደሆኑ የእግዚአብሔር ምድርን የመግዛት መርህን ተከትለው ህዝባቸውን በማስተዳደር ዋና ጉዳይ ላይ ነበር ሲሰሩ የኖሩት፡፡

አዲስ ኪዳን ላይ ከዚህ የተለየ ነገር አናይም ፡፡ አዲሱ ነገር የእግዚአብሔር ህዝብ የእግዚአብሔርን መርህ ተከትለው ባለመሄዳቸው ምክንያት እግዚአብሔር መንግስቱን እንደገና ለመምራት ከህዝቡ ጋር አብሮ መሆኑን ያወጀበት ጊዜ መሆኑን ነው የምናገኘው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር መንግስት ምን ምን ማካተት እንደሚገባው የቀደሙት የእግዚአብሔር መንግስት አስመስለው የራሳቸውን ፍላጎት የሚያራምዱበት ዘመን ማብቃቱን በማወጅ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት በህዝብ መካከል መሆኑን የመንግስቱን ርእዮተ ዓለሙን ደግሞም ምን ምን እንደሆነ ማወጅንም ይጨምር ነበር፡፡ ዋና ጉዳዮቹን የሚያስፈጸሙበትን እቅድና አሰራር በመዘርጋቱ በዘመኑ ከነበረው መንግስታዊ ተቋዋም ለሞት የሚያበቃ ግጭት ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ይሁንና መንግስቱን ከመመስረት አልመለሰውም ሃዋሪያት ስራ ላይ የእርሱ ተከታዮች ትምህርታቸውን ሲሰሙና ሲያሰሙ እነዚህ መንግስትን የሚገለባብጡ ተብለው ክስ ቀርቦባቸው ነበር፡፡ በሓዋሪያት ስራ 17፡6ለ ጀምሮ እንዲህ ይላል

«እነዚህ ዓለምን ሁሉ ያወኩ ሰዎች አሁን ደግሞ ወደዚህ መጥተዋል! 7ኢያሶንም ተቀብሎአቸዋል፤

‹ኢየሱስ የሚባል ሌላ ንጉሥ አለ› እያሉም የሮምን ንጉሠ ነገሥት ትእዛዝ ይቃወማሉ።» 8ሕዝቡና
የከተማው ባለሥልጣኖች ይህን በሰሙ ጊዜ ተሸበሩ። 9ኢያሶንንና ሌሎቹንም ዋስ አስጠርተው
ለቀቁአቸው።

ለዚያ ዘመን ሓዋሪያት የፓለቲካው መዋቅር የኢኮኖሚው ፍሰት ወይም የህይወት ፍልስፍና እንዳለ ከኢየሱስ አስተምህሮት የማይስማማ ስለነበር እራሳቸው የሚገዙለት ንጉስ እንደነበራቸው ሓዋሪያት አስተምረው ነበር፡፡ አንባቢዎች እንድንገነዘበው የሚፈለገው እውነት የኢየሱስ ቀላል የሚመስል የህይወት ፍልስፍና ትላልቅ ነገስታትን የሚንጥ ነበር፡፡ ብዙዎቹ እንደምታውቁት ንጉስ ያለመንግስት መንግስት ያለፍልስፍና የሚቆሙ ጉዳዮች አይደሉም ፡፡ ሓዋሪያቶች በሄዱበት ዘመንም ምንም የተኮሱት ጥይት የታጠቁት መሳሪያ አልነበራቸውም፡፡ ይሁንና ያላስፈቱት የመሳሪያ አይነት ያላወረዱት ስልጣን አልነበረም ፡፡ ለብዙዎች የቅርብ እሩቅ የሆነ እውነት ቢሆንም ...የኢየሱስ ቃሎች ህያውና የሚሰሩ ኢየሱስም አብሮአቸው ዓላማቸውን ሊያስፈጽም ስለሚገኝ በዕምነት የሚነገሩ ቃላቶች በእምነት የሚታወጁ ቃሎች ማንኛውንም የፀና የአመጽ ጉልበጽ የማፍረስ ብቃት ነበራቸው አላቸው ይኖራቸዋልም፡፡

የመንግስቱ አስተምህሮቶች ሰዎች ሁሉ ሃጢአት ሰርተዋል ንሰሃ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ ልባድርጉ ሃጢአተኛ ራስ ወዳዶች በመሆናቸው ብቻቸውን ለምንም አይነት ንብረት ታማኞች መሆን አይችሉም፡፡ ስለዚህ ከፍተኛ ህጋዊ ቁጥጥር ያስፈልጋቸዋል፡፡ በድሆችና በባለ ብዙ ሃብት ክምችት መካከል ያለው ከፍተኛ ልዩነት የራስ ወዳድነት መጠን ብዛትና ያንን ዓላማ ለማከናወን የሚጨፈለቁ የህግ ብዛቶችን ያስጠነቅቁናል፡፡ ድሆችን ገፈዋቸዋል ድሆችን ባሪያ አድርገዋቸዋል ይህ መቀየር አለበት፡፡ ለመቀየር የሚኬድበት መንገድ ግን በፍቅርና በፍጹም ትህትና ነው፡፡ ራስን አሳልፎ በመስጠት እንጂ ለራስ ምቾት ሲባል ሌሎች ህይወትን እንዲሰጡ ያለማስገደድን እንደ ርእዮተ አለምን ተከትሎ ነው፡፡ ኢየሱስ በዚህ የተሳካለት ንጉስ ሲሆን ደቀመዝሙርቶቹም የተሳካላቸው ነጻ አውጪ ነበሩ ፡፡ ሓዋሪያው ጳውሎስ አለምን የነቀነቀ ትምህርትን ያቀረበ ቢሆን ማነንም ያልዘረፈ ያለውን ሁሉ ለሰው ልጆች በመስጠት ያሳለፈ ነበር፡፡ በመጨረሻው ደብዳቤው ላይ አንድ ልብን የሚነካ ደብዳቤ ጽፎ ነበር ለጢሞቲዎስ መጽሓፍቱንና ካፓርቱን ይዘኽልኝ ና ሲል

.... ትትት ሰሰሰትመ...መጣ በጢሮአዳ ትትት የተውኩትን ትትት በርኖስ ጥቅል መጽሓፍቱን አምጣልኝ ...ትትት....2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡14

ብዙ ሺ ኪሎሜትሮች አቋዋርጦ ጣሊያን ውስጥ እንዲያመጣለት ይለምን ነበር፡፡ ዛሬ ጣሊያኖች ብዙ አደባባይ ገንብተውለት የሚያወድሱት ጳውሎስ ለነጻነታቸው በብርዳቸው ተሙቶላቸዋል፡፡ እየተጎዳ ነጻ የሚያወጣ ንጉስ ነጻ አውጪ የማይደበዝዝ ነጻነት ከክብር ጋር ማቅረብ የሚችል ርዕዮተ ዓለም አለው፡፡ ርዕዮተ ዓለሙ ለሌላው ለመጎዳት መፍቀድ እንጂ ለራስ ፍላጎትና ህልም ሌላውን መጉዳት መርሁ ሆኖ አያውቅም ፡፡ ሌላውን በመጉዳት ርዕዮተ አለማችሁን ለምትጭኑ ኢየሡስ እንዲህ ይላችሁአል ፡፡ ኢየሡስ እናንተ ሸክም የከበዳችሁ ደካሞች እኔ አሳርፋችሁአለሁ፡፡ ሠይፋችሁን መልሱ ..ሰይፍ የሚያነሱ በሰይፍ ይጠፋሉ! ሰይፋችሁ ወደ ሰገባ ይመለስ ድሆችን ለመዝረፍ የገተራችሁትን ሰይፍ መልሱ ንሰሃ ግቡ የማታሸንፉት ትልቅ አምላክ ባትሰሙት ሊያደቃችሁ ተዘጋጅቶአል፡፡ ክፉ የሰራ ከእንግዲህ ክፉ አይስራ የሰረቀ ከእንግዲህ አይስረቅ እርግጠኞች ሁኑ አንድ ነብስ ነው ያላችሁ የሌሎችንም ነብስ የመኖር ፍላጎት አክብሩ ፡፡

በኢየሱስ ተከታዮች ዘንድ የቃላቶች ብርታት ይታወቅ ስለነበር ጸልዮ ከማንኛውም ዘመን ካፈራቸው መሳሪያዎች የሚበልጠውን የማጥቂያና መከላከያ መሳሪያ ጸሎትን ቃል አውጥቶ መናገርን ማወጅን አድልኦን ጸንቶ መቃወምን ተቃውሞው ሰውን ክቡር ህይወት ምን እንደሚመስል ለዓለም አጎናጽፈዋል፡፡ ከቀደሙት የእምነት አባቶች ላይ የሰራ መንፈስ እንዲወርሰን እኛም እንጸልያለን አይናችን ከፍተን እንጸልያለን!

**ሓይማኖት ከሃይማኖትነት አልፎ የሚሄደው ወንጀል የሚሆንበት ምን ሲሆን ነው ?**

በአጭር ቃል መንግስት በህገመንግሰት ይመራል፡፡ እምነት በሚመራበት መጽሐፍ ቅዱስ ወይንም በእምነቱ መተዳደሪያ መፅሃፍ ይመራል ፡፡ ይሁንና ህገመንግሰቱ የሚለው ቀርቶ በኛ መጽሓፍ ሓገር ይመራ ሲባል ቤተክርስቲያን በፓለቲካ ሳይሆን በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ ተገባ ሊባል ይችላል ፡፡ ፓለቲካ የሌለው ተቋዋምም የለም መንግስት ብቻ ሳይሆን እምነት ተቋዋናት ፓለቲካ አላቸው የሚያሳስቱ ቃላት ሊሻሻሉ ባለስልጣኖችም በዚህ ሰዎችን እንዳያሳስቱ መጥንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ የሃገሪቱ ህገመንግስት ሃያማኖት በመንግስት መንግስት በሐይማኖት ጣልቃ አይገባም ነው የሚለው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሌላው ቀርቶ ሐገር በኛ መጽሓፍ ይመራ የሚል ሃሳብ ቢንሸራሸርም ችግር የለውም ፤ በዚህ ካልተመራ እኔ አስገድዳለሁ ብሎ ግፊት ሲጀምር አክራሪነት ተከናወነ ማለት ነው በፓለቲከኞቹ ላይ ሳይሆን በህገመንግስቱ ላይ ወንጀል ይሆናል፡፡

መከራከር መወያየት ይቻላል ማስገደድ ግን ፈጽሞ ህገመንግስትን መናድ ይሆንብናል፤ ህገመንግስቱን አክብሮ ግን መሻሻል ያለበትን እንኩዋን አንስቶ ጥያቄ ማቅረብ ፊርማ ማሰባሰብ የጠያቂው ብዛትና ከሌሎች ህጎች ጋር ያለው ዝምድና ታይቶ ማስተካከል እስከሚቻል ድረስ ወንጀል አይሆንም አልፎ ተኬደም አይባልም፡፡ አንዲት ስንዝር የማስገደድ ቃል ሃይል ለመጠቀም ማሰብ ግን ህገመንግስት በሓይል የማፍረስ ወንጀል ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔርም ላይ የሚደረግ አመጽ አድርገን ልንገነዘበው እንችላለን፡፡

መንግስትም (ሁሉም ሰው የመንግስት አካል ነው ብቸኛ መንግስት የሆነ ሰው ወይም ቡድን የለም) ህገመንግሰትን መሰረት ባላደረገ እቆምለታለሁ የኔ ነው እጠብቀዋለሁ የሚለው ምንም ፕሮግራም አይኖረውም፡፡ የቁዋንቁዋቾችን ውሱንነት የሚያሻማው የመንግስት ማንነትና ምንነት (ለዘመናት የመጣው ሉኣላዊ ክብር የሚካተለቱ የሃገሪቱ ታሪክ እውነታ ቅርጽ ድንበር ኅዝቡና የለህገመንግስት መሻሻል ሊነኩ የማይችሉ ሁኔታዎችን ሲቀር) የመንግስትን መ መዋቅር ተቀብሎ መንግስትን የሚመራው አካልም ፓርቲ ወይም ጥምር ቡድን በህገመንግሰቱ የተሰጠውን የስራ ሃላፊነት በአግባቡ ማከናወን ብቻ ነው ሓላፊነቱ ፡፡ የፓርቲ ፕሮግራሞች ዋና አጀንዳ ሊሆን እይችልም ፡፡የፓርቲ ፕሮግራም የራሱ የፓርቲ አባላቶች ጉዳይ እንጂ የሃገር ጉዳይ መሆን አይችሉም፡፡ የሃገር ጉዳይ ከ ህገመንግሰት ውስጥ የሚወጡ ፓሊሲዎች ብቻ ለጋራ ብልጽግና ከህገመንግስቱ ውስጥ የሚመዘዙ ሆኔታዎች ብቻ ናቸው የመንግስት ሃላፊነቶች! ስለዚህ የተለያዩ እሴቶች ያሉአቸው የአንድን ሃገር ህዝብ ፍላጎት አቻችሎ መምራት ነው መታዘዝ ነው ሃላፊነታቸው!

አይናችንን ገልጸን አሁን እንጸልያለን፡ ቁጥሮችን አንዳንዴ ያልታዩትን ስለሚያሳዩን እነርሱን እያሰብን እንጸልያለን ፕሬዘዳንታችን የተዘጋጀላቸው የየወር ኪራይ ለሃገሪቱ ህዝብ የሚያስቡ መሪዎች መኖራቸውን የሚያጠራጥር ቀመር አስቀምጠውልናል፡፡ የሪፓርተርን ጋዜጣ ያነበበ ሰው እንዳለው ይህ አሃዝ የሳንቲም ቤቱን አሳስተው ቢሆን ነው እንጂ እንዴት 350.000 ብር የወር ኪራይ ኢትዮጵያ መንግስት በግልጽ ይህን ያህል ባጀት መመደብ ይችላል ብዬ ልጠርጥር ብሎ ነበር ፡፡ ቢያስፈልግ ቤተመንግስት ሰርተው አያስረክቡም የአንድ አመቱን ወይም የሁለት አመቱን ቤት ኪራይ በብድር ተሰጥቶ ያሉትን አይነት ምቾት የሚተካ ቤተመንግስት አይሰራም፡፡ ወይስ ለብድር አይታመኑም ይሆን? የሁለት አመቱ ኪራይ 8 ሚሊዮን አራት መቶ ሺ ብር ነው ለቤት ኪራይ ብቻ፡፡ የአጃቢ የሰራተኛ የቢሮ አስፈላጊዎችን ወጪ ለእድሜልካቸውና ወደ ወራሾቻቻ የሚተላለፉ ሆነውም ነው ወርሃዊ ወጪዎቹ፡፡ ሌላው ያንን ጽኍፍ ያነበበ እንግዲህ ቤቱን የሚያከራየው ሃገሪቱን እጅ ጠምዝዞ የሚያስፈርም ሰው አለ ማለት ነው ሲል ጠቁሞአል፡፡



እንግዲህ ብዙዎች በስህተት እንደሚተረጉሙት ይህ ፓለቲካ ሳይሆን በጋራ እግዚአብሔር በሰጠንና በፈጠረን ምድር ላይ አስተዳደር ላይ የሚሰጥ አስተያየት ሲሆን ኢትዮጵያ ከአድሎ የጸዳች የሁሉም ኢትዮጵያዊ ክብር የሚጠበቅባት ሓገር እንድትሆን የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ፓለቲካ(የማስተዳደር ጥበብ) የኢትዮጵያውያን ህገመንግስት የህግ የበላይነት የሚከበርባት ሰዎች እኩል የሚሆኑባት የኑሮ ልዩነት የሚጠብባት ምድር እንዲሆን እንጸልያለን፡፡ በዚህም ላይ ፍርድን በማጣመም የድሆችን ጣር ለማብዛት የሚሰራ አጋንንታዊ መዋቅር እንዲፈርስ እንጸልያለን! እመኑኝ ኢየሱስ ይህንን ጸሎት ይሰማዋል ያደርገዋል ያሳየናል!